# <u>የጽ/ቤት ግንባታ ለማኅበሩ አገልግሎት መፋጠን</u>

ማኅበራችን ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ በርካታ ሥራዎችን እንዲከናወንና እያከናወነ እንዳለ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ አገልግሎቱን በስፋትና በተቀላጠፈ ሁኔታ ለማስኬድ የጽ/ቤት ግንባታው ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ መሆኑ እሙን ነው፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን  በሀገሪቱ ካሉት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ማሠልጠኛዎች የሚገቡ ክርስቲያን ተማሪዎች ከዘመናዊ ትምህርት ጐን ለጐን የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት በማስተማር ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ በአሁኑም ወቅትም በ*210* የግቢ ጉባኤያት  ተልእኮውን በመወጣት ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋት ረገድ ምእመናን የቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት፣ሥርዐትና ትውፊት እንዲያውቁ እንዲጠብቁ ማድረግና የቤተ ክርስቲያኒቱን ሐዋርያዊ አገልግሎት በማጠናከር ረገድም የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ጥሩ የማነሳሳት ሥራ እያከናወነ ይገኛል፡፡ ከግቢ ጉባኤያት የሚወጡና ትምሕርታቸውን ያጠናቀቁ ተማሪዎች በተሰሩበት የሥራ መስክ በሔዱበት አካባቢ ቅድስት ቤተክርስቲያንን ባላቸው ዕውቀትና ሞያ እያገለገሉ  ግቢ ጉባኤያትን በማስተባበር ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልማት አስተዋጽኦ ለማድረግ *40* ማዕከላትን በማደራጀት የአገልግሎት አድማሱን አስፍቷል፡፡

አባላት ለስራም ሆነ ለትምሕርት በሚንቀሳቀሱባቸው የውጭ ሀገራትም ጭምር የማእከላቱን እንቅስቃሴ በማስፋፋ ላይ ይገኛል፡፡ እንዲሁም የግንኙነት ጣቢያዎች በመከፈት ላይ ናቸው፡፡ በአሁኑ ወቅትም በሰሜን አሜሪካ፣ ካናዳ፣ አውሮፖና ኬንያ ማዕከላትን በማቋቋም በካምፖላ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ እስራኤልና አካባቢዋ እንዲሁም ጅቡቲ ደግሞ የግንኙነት ጣቢያዎችን በመክፈት አገልግሎቱን በማጠናከር ላይ ይገኛል፡፡

በዋናው ማዕከል የግቢ ጉባኤያትና አባላትን በማስተባበር የሚሰጣቸው በርካታ አገልግሎቶቹ በርካታ ሲሆኑ፤ ለአገልግሎት አመቺ የሆኑ መዋቅሮች በመዘርጋት ዋና ክፍሎችን በማደራጀት በትምሕርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት በጋዜጣ፣ በመጽሔትና መጻሕፍት ኅትመት፣በቅዱሳት መካናት ላይ የተለያዩ የልማት ፕሮጀቶችን በማከናወንና የአብነት ት/ቤቶች ርዳታ፣ ኤች አይቪ ኤድስ መከላከል እንዲሁምበልማት ተቋም ጨምሮ የንዋየ ቅድሳት ምርትና ሥርጭት ከፍተኛ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ አገልግሎቱቹም በሙሉ በመደበኛና

በቱሩፋት አገልጋዮች የሚከናወን ነው፡፡ በአሁኑ ወቅትም ከ300 በላይ መደበኛ አገልጋይ እና 10,000 በላይ የቱሩፋት አገልጋዮች ይሳተፋሉ፡፡ የማኅበሩ አገልግሎት ከጊዜ ወደጊዜ በከፍተኛ ፍጥነት እየሠፋ የመጣ ሲሆን 40 ማዕከላትን 400 ወረዳ ማዕከላት፣ 210 የግቢ ጉባኤያት በሀገር ውስጥ ሲኖሩ ከኢትዮጵያ ውጭም አምስት ማዕከላትና አምስት የግንኙነት ጣቢያዎች በመምራት ላይ ይገኛል፡፡ እነዚን የአገልግሎት ከፍሎች ለመምራት፣ ለማደራጀትና ለማስተባበር ምቹ የአገልግሎት ቦታ አለመኖሩ አገልግሎቱን ፈታኝ በማድረጉ የጽ/ቤት ግንባታው ወሳኝ እንዲሆን አድርጐታል፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን በ5ኛው ጠቅላላ ጉባኤ ባሳለፈው ውሳኔ አባላቱንም ለበለጠ አገልግሎት ያነቃቃበት ማኅበሩ ጽ/ቤት እንደሚያስፈልገውም በማመን ሕንፃ ለመገንባት አባላቱ በያሉበት የአንድ ወር ደመወዛቸውን ለጽ/ቤት ግንባታ ለመስጠት የወሰኑበት ጊዜ አይዘነጋም፡፡ በእግዚአብሔር ፈቃድ ይኸው የጽ/ቤት ግንባታ ሚያዝያ 5 ቀን በ1999 ዓ.ም ተጀምሮ አባላቱና የማኅበሩን እንቅስቃሴ የሚደግፉ በጎ አድራጊ ምእመናን በሚያደርጉት የገንዘብ፣ የቁሳቁስና የሞያ እገዛ እንዲሁም ጸሎት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የጽ/ቤት ግንባታው አንድ ብሎ ተጀምሮ ሰባተኛው ፎቅ ላይ ደርሷል፡፡ ለሕንፃው እዚህ መድረስ የአባላት መዋጮ የምእመናን እገዛና ጸሎት ታክሎበት አጽመ ሕንፃውን ለማጠናቀቅ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ደርሰናል፡፡ በዚህ የግንባታ ሂደት ውስጥ በርካታ ውጣ ውረዶችንና የማይዘነጉ ፈተናዎችን አሳልፏል፡፡

የጽ/ቤት ሕንፃ የዲዛይን ለውጥ ከማድረግ ጀምሮ የግንባታ ቁሳቁስ ቀን በቀን በከፍተኛ ፍጥረት እየጨመረ መሄዱ፣ ቃል የተገባውን ገንዘብ በፍጥነት አለማግኘት፣ ማዕከላትና ግቢ ጉባኤያት የሚጠበቅባቸውን መዋጮ በወቅቱ አለመስጠት የሚጠቀሱ ችግሮች በመሆናቸው የጽ/ቤት ግንባታው በታለመለት ዕቅድ መሠረት ሊጠናቀቅ አልቻለም፡፡

የጽ/ቤት ግንባታው ከሕንፃው ንድፍ ጀምሮ እስከ አሁን የደረሰበት ደረጃ ድረስ ማኅበሩ በግቢ ጉባኤያት ያስተማራቸው አባላቱ ያበረከቱት የሞያ እገዛ ከፍተኛ ነው፡፡ ሕንፃውን ለማነጽ ገቢ ማስገኛ በፕሮጀክቶች ተነድፈው የሚከናወኑ መርሐ ግብሮች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህም የእግር ጉዞ፣ የገዳማትና አድባራት ጉብኝት፣ የምሳ ግብዣና የበጎ አድራጊዎች የገንዘብና ቁሳቁስ ልገሳ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ፕሮጀክቶች ውስጥ አብዛኞዎቹ ከፍተኛ ውጤት ተገኝቶባቸዋል፡፡

በዘንድሮ 2002 ዓ.ም የአጽመ ሕንፃውን ድምድማት የማጠናቀቂያ ሥራዎች ለማከናወን የጽ/ቤት ግንባታ አሠሪ በከፍተኛ እንስቅቃሴ ላይ ይገኛል፡፡ ይኸውም ከላይ አልሙንየም የማልበስ ሥራና እስከ ሁለተኛ ፎቅ የማጠናቀቂያና ጽዳት ሥራዎችን ማከናወን ናቸው፡፡



ማኅበሩ በኪራይ የሚያወጣውን ገንዘብ በማዳን የሚያከናውናቸውን ልማቶች ለማፋጠን ይረዳው ዘንድ ሕንፃው ባይጠናቀቅም፤ በጅምር ሕንፃ ውስጥ በመግባት በአንደኛው ፎቅ ላይ ዋናውን ጽ/ቤት አድርጓል፡፡ አዲስ አበባ ማዕከልንም ወደፊት የመኪና ማቆሚያ በሚሆነው ምድር ቤት በማድረግ በአመት ከ150,000.00 ብር በላይ ለኪራይ ከማውጣት መታደግ ተችሏል፡፡ ይህ ሲባል ግን ችግሮች የሉም ማለት አይደለም፡፡ ግንባታው በሚከናወንበት ጊዜያት በዋናው ጽ/ቤትም ሆነ በአዲስ አበባ ማዕከል ክፍሎች ከላይ ፍሳሽ ውኃ በመግባት ሰነድን ዶክሜንት ከማጥፋት አንስቶ እስከ ኮምፒውተርና ኘሪንተር ማበላሸት ደርሷል፤ ምንም እንኳ ከውስጥ ያለው ቅዝቃዜ ለአገልጋዬች የጤና ሁኔታ ተጽዕኖ እያደረሰ ቢሆን እንኳ አባላቱ ካላቸው ቁርጠኝነት የተነሳ አገልግሎቱም ሆነ ግንባታው ሳይስተጓጐል ቀጥሏል፡፡

በአሁኑ ወቅት ዐበይት የሆኑ መሠረታዊ ክንውኖችን እየተወጣን ቢሆንም፤ ሕንፃውን ዛሬም ለተሻለ አገልግሎት ለማብቃት የእኛን ከፍተኛ ትጋትና ጥረት ይጠይቃል፡፡ የጽ/ቤት ግንባታው የአባቶቻችንን አደራ ለመወጣት፣ ይበልጥ የተነሣንበትን የአገልግሎት ርእይ እውን ለማድረግ፣ በተሻለና በጠነከረ መልኩ አገልግሎት መስጠት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የስብከተ ወንጌልን አገልግሎት ለማፋጠንና የቤተ ክርስቲያንን ርእይ እውን ለማድረግ የጀመርነውን እንድንፈጽም ትናንት ከጎናችን ሆናችሁ የአቅማችሁን በማገዛች በማኅበሩ ታሪክ ሁሌም የሚዘከር ሲሆን ዛሬም እንደ ትናንቱ በጸሎታችሁ፣ በዕውቀታችሁ እና በገንዘባችሁ ከጎናችን እንድትሆኑ አደራችን ጥብቅ ነው፡፡

**ቅስቀሳና ገቢ አሰባሳቢ ኮሚቴ**

# <u>የማኅበረ ቅዱሳን ጽ/ቤት ግንባታ</u>

## አምላክ ሆይ! እጄን አበረታ.... ነህምያ 6÷9



***እንደ ልዑል እግዚአብሔር ፈቃድ***

***ዛሬ እዚህ ላይ ደርሰናል።***




***ነገ ደግሞ ይህንን እናያለን!!!***

የማኅበሩን ጽ/ቤት ለመገንባት በሚደረገው ርብርብ በየማዕከሉ የሚገኙ የማኅበሩ አባላት፣ ግቢ ጉባኤያት በጎ የሆነውን የማኅበሩ ተልእኮ ተረድተው ከጐናችን ለሚያግዙን ምእመናን ሁሉ ላደረጋችሁት መንፈሳዊ ልገሳና ትብብር ልዑል እግዚአብሔር በረድኤቱ ይጐብኛልን እንላለን። ዛሬ ሰባተኛው ፎቅ ላይ ደርሰናል፤ ነገ በእናንተው እገዛና እርዳታ ግንባታውን እናጠናቅቃለን!!!

ማኅበረ ቅዱሳን ጽ/ቤት ግንባታ

ንግድ ባንክ ሥላሴ ቅርንጫፍ

**የባንክ ሒሳብ ቁጥር 75838**

*የጽ/ቤት ግንባታ ቅስቀሳና ገቢ አሰባሳቢ ኮሚቴ*